የቤተሰብ የመረጃ ሰነድ

# ጤናማ በመሆን እና ባለመሆን መካከል መሆንን የሚያሳይ ውጤት፡ የደም ምርመራ ውጤት ማሳወቂያ

የሚኔሶታ አዲስ የተወለዱ ህጻናት ምርመራ ፕሮግራም

**Borderline Newborn Screening Result, Family Fact Sheet—Amharic**

## ጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ ወሰን አዲስ የተወለዱ ህጻናት ምርመራ ውጤት

### አዲስ የተወለዱ ህጻናት ምርመራ የተገኘው ምን ነበር?

በወሊድ ወቅት የተወሰደው አዲስ የተወለደ ህጻን ምርመራ ልጅዎ የጤንነት ህኔታ በጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ ወሰን መካከል የሚገኝ መሆኑን ያሳያል።

### ጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ ወሰን መካከል ያለ ውጤት ማለት ምን ማለት ነው?

ጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ ወሰን መካከል ያለ ውጤት ማለት ምርመራው ጤናማ እና ጤናማ ያልሆነ በሚባለው መካከል ያለ ማለት ነው። የሚከተሉትን ጨምሮ ውጤቶች ጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ መካከል በሚገኝ ወሰን ውስጥ እንዲካተቱ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡

- ህጻኑ ሲወለድ ሲል የተለያዩ ነገሮች ስለሚስተካከሉ በዚያን ወቅት በህጻኑ አካል ውስጥ የሚከሰቱ መደበኛ ለውጦች
- ያለጊዜያቸው የሚወለዱ ህጻናት (የመወለጃ ጊዜያቸው ከመድረሱ በፊት)
- በአስቸጋሪ ወይም አስጨናቂ ወሊድ የተወለዱ ህጻናት
- ለሙቀት እና ርጥበት የተጋለጡ የደም ጠብታዎች
- ለእናትየው ወይም ለህጻኑ የተደረጉ የተወሰኑ ህክምናዎች

<u>አብዛኛውን ጊዜ ውጤቱ ጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ ወሰን መካከል የሚሆንበት ምክንያት ግልጽ አይደለም።</u>

### ቀጥሎ ምን ይሆናል?

የህጻኑ ሀኪም አዲስ የተወለደ ህጻን ምርመራ በድጋሚ እንዲደረግ ያዛል። ጤናማ እና ጤናማ ባልሆነ ወሰን መካከል የሚገኝ የምርመራ ውጤት ያላቸው አብዛኛዎቹ ህጻናት በድጋሚ በሚደረጉ ምርመራዎች ጤናማ መሆናቸውን የሚያሳይ ውጤት ያገኛሉ። ይሁን እንጂአዲስ በተወለደ ህጻን ምርመራ የሚገኙት የጤና ችግሮች አሳሳቢ በመሆናቸው፣ ምርመራውን በድጋሚ ማድረግ እና ልጅዎ የጤና ችግር የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

### ልጄ በድጋሚ የተደረገ የምርመራ ውጤት እንዲኖረው ላደርግ የምችለው እንዴት ነው?

የልጅዎ የደም ናሙና አንድ ጊዜ የምርመራ ቤተሙከራ ከደረሰ በኋላ፣ ምርመራው ወድያውኑ ይጀመራል፣ ነገር ግን በርካታ ቀናት ሊወስድ ይችላል። የምርመራው ውጤቶች ለልጅዎ ሃኪም ወይም ክሊኒክ ይሰጣል።

### በድጋሚ በተደረገው ምርመራ ጤናማ ቢሆንስ?

ውጤቶቹ ጤናማ መሆኑን የሚያሳዩ ከሆነ፣ ልዩ ምርመራ ወይም ህክምና ማድረግ አያስፈልግም። ጤናማ በመሆን እና ባለመሆን መካከል ካለ ውጤት ጋር በተያያዘ የሚደረግ የጤና ክብካቤ ከዚህ በኋላ አያስፈልግም። ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ ከህጻኑ ሃኪም ጋር ይነጋገሩ።

### በድጋሚ በተደረገው ምርመራ የተገኘው ውጤት አሁንም ጤናማ በመሆን እና ባለመሆን መካከል ወይም ጤናማ አለመሆኑን የሚያሳይ ቢሆንስ?

በድጋሚ በተደረገው ምርመራ የተገኘው ውጤት በድጋሚ ጤናማ በመሆን እና ባለመሆን መካከል ወይም ጤናማ አለመሆኑን የሚያሳይ ከሆነ፣ ልጅዎ ስለሚያስፈልገው ተጨማሪ ምርመራ ወይም ህክምና ሃኪምዎ ያሳውቅዎታል።

### መርጃዎች

**የዘረመል መነሻ ማጣቀሻ፡-**
http://ghr.nlm.nih.gov

**Save Babies Through Screening Foundation:**
www.savebabies.org

**የልጅ የመጀመሪያ ምርመራ፡-**
www.babysfirsttest.org